የትምህርት ተቋማቱ

አወሊያ ቁጥርአንድ 1ኛ/ደ/ት/ቤት ፒያሳ

አወሊያ ቁ.አንድ 1ኛ/ደ/ት/ቤት ፒያሳ በ1944 የተመሰረተው ሲሆን ያኔ በእነኡስታዝ አህምድ ጊዜ በሶስት ክፍል ፤ የተማሪ ከፍያም ከ 5-10 ብር የነበረው ይህ ትምህርት ቤት በአሁኑ ስዓት ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያለው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት በመሆን በርካታ አንቱ የተባሉ ባለሙያቸውን አስተምሮ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ከፍተኛ ደረጃ ደርሰው በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር በመሆን ሀገራቸውንና ህዝባቸውን በማገልግል ላይ ይገኛሉ።

በ በዚህ ትምህርት ቤት ወንድ 196 ሴት 200 በድምሩ 396 ተማሪዎች ያሉት ሲሆን ከነዚህ መካክል 31 ተማሪዎች በነጻ፤14 ተማሪዎች በግማሽ እንዲሁም 353 ተማሪዎች በሙሉ ክፍያ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ።የተማሪዎች ወርሃዊ ክፍያም ከ300-400 ብር ነው።

በ3 መምህራን ስራውን የጀመረው ይህ ትምህርት ቤት ዛሬ 18 መምህራንና 14 ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አሉት። በአሁኑ ስዓት በት/ቤቱ ያለውን የገንዘብ ገቢና ወጪውን በተመለከተም ከተማሪዎች ወርሃዊ ክፍያ የሚሰበሰብ ብር 125.601ሲሆን ለዚሁ ት/ቤት ብቻ ወጪ የሚደረግ ለደመወዝ ብር 176.357 ለስራ ማስኪጃ ደግሞ ብር 16.911 ራሱን ለመቻል ብር58.668 ገቢ ማስገኘት ይጠበቅበታል። ት/ቤቱ መጠነኛ ከጣሪያና ከቀለም እድሳት ውጪ በቀድሞው ሁኔታ ባለበት እንዳለ ነው።





አወሊያ ፒያሳ 1ኛ ደ/ት/ቤት

አወሊያ ቁ.1 1ኛደ/ት/ቤት አስኮ በ1974

በ1974 ሰራ የጀመረው አወሊያ ቁ.1 አስኮ 1ኛ/ደ/ት/ቤት ወደ ሰላሳ ስምንት አመታት እድሜ ያስቆጠረ ሲሆን 27 የመማሪያ ክፍሎች ፤ሁለት ብሎክ የአስተዳድርና የመምህራን ማረፊያ አለው። በአሁኑ ስዓት በትምህርት ቤቱ ወንድ 686 ሴት 762 በድምሩ 1448 ተማሪዎች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ መካከልም 210 ተማሪዎች በነጻ፤55 ተማሪዎች በግማሽ፤1188 ተማሪዎች ሙሉ ክፍያ በማስከፈል ያስተምራል። የተማሪዎች ወርሃዊ ክፍያ ከ1-5ኛ 400ብር፣

ለ7ኛ እና 8ኛክፍል 450 ብር ነው።በትምህርት ቤቱ ወንድ 36 ሴት 20 በድምሩ 56 መምህራን እና ደግሞ ወንድ 8 ሴት 12 በድምሩ 20 ድጋፍ ሰጪ በአጠቃላይ 76 መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ይገኛሉ። በአሁኑ ስዓት በት/ቤቱ ያለውን የገንዘብ ገቢና ወጪ በተመለከተም ከተማሪዎች ወርሃዊ ክፍያ የሚሰበሰብ ብር 346.519 ሲሆን ለዚሁ ት/ቤት ብቻ ወጪ የሚደረግ ለደመወዝ ብር 402.353 ለስራ ማስኪጃ ደግሞ ብር 35.000 ራሱን ለመቻል ብር 90.834 ገቢ ማስገኘት ይጠበቅበታል፡፤





ከአስራ አምስት አመታት በኋላ በአወሊያ የቀድሞ ተማሪዎች ትብብር 2012 የትምህርት ዘመን የታደሰ

አወሊያ ቁ.1 አጸደ ህጻናት

አስራስድስት አመቱን ያስቆጠረው ይህ አጸደ ህጻናት ት/ቤት በ1996 ነበር የተመሰረተው። ትምህርት ቤቱ ካሉት መካከል በትምህርት አሰጣጡ ጥራቱ ተመራጭ ትምህርት ቤት የሚባል ነው።

በአሁኑ ስዓት በትምህርት ቤቱ ወንድ 270 ሴት 280 በድምሩ 552 ተማሪዎች ያሉት ሲሆን ከነዚህ መካካል 110 ተማሪዎች በነጻ ፤13 ተማሪዎችን በግማሽ ፤426 ተማሪዎች በሙሉ ክፍያ ተቀብሎ ያስተምራል። የተማሪዎች ወርሃዊ ክፍያም ብር450 ነው። በትምህርት ቤቱ 26 መምህራንና 24 ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ይገኛሉ።በአሁኑ ስዓት በት/ቤቱ ያለውን የገንዘብ ገቢና ወጪውን በተመለከተም ከተማሪዎች ወርሃዊ ክፍያ የሚሰበሰብ ብር 161.704ሲሆን ለዚሁ

ት/ቤት ብቻ ወጪ የሚደረግ ለደመወዝ ብር 166.141 ለስራ ማስኪጃ ደግሞ ብር 16.911 ራሱን ለመቻል ብር 18.772 ገቢ ማስገኘት ይጠበቅበታል፡፡




አወሊያ ቁ.1 አጸደ ህጻናት ት/ቤት

አወሊያ ቁ.1 2ኛ ደ/ት/ቤት አስኮ

አወሊያ ቁ.1 2ኛ ደ/ት/ቤት አስኮ በ1980 ስራ የጀመረ ሲሆን (የዘንድሮን ጨምሮ ለ 32ኛ ጊዜ 12ኛ ክፍል አጠናቀው ለከፍተኛ ትምህርት በማብቃት በርካታ ዶክተሮችን፤ ኢንጅነሮችን፤ የህግ ባለሙያዎችን ና በሌሎች የሙያ መስኮች በማብቃት በሀገር ውስጥና በውጪ ራሳቸውን፤ ህዝባቸውንና ሀገራቸውን በማገልገል ላይ ይገኛሉ)





አወሊያቁ.1፣2ኛና መሰናዶ ትምህርት ቤት ለ2012 ት/ዘመን ባማረ ሁኔታ ታድሷል፡፡

በአሁኑ ስዓት ወንድ 237 ሴት 336 በድምሩ 573 ተማሪዎች ተቀብሎ የሚያስተምር ሲሆን 78 ተማሪዎችን በነጻ ፤13ተማሪዎችን በግማሽ ፤475ተማሪዎችን ደግሞ በሙሉ ክፍያ

በማስተማር ላይ ሲሆን ወርሃዊ ክፍያቸውም ከ9-10ኛ ላሉ ብር450 ከ11-12ኛ ክፍል ብር500 ነው።

በትምህርት ቤቱም 36 መምህራንና 32 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 68 መምህራንና ሰራተኞች ይገኛሉ።በአሁኑ ስዓት በት/ቤቱ ያለውን የገንዘብ ገቢና ወጪውን በተመለከተምይገኛሉ።በአሁኑ ስዓት በት/ቤቱ ያለውን የገንዘብ ገቢና ወጪውን በተመለከተም ከተማሪዎች ወርሃዊ ክፍያ የሚሰበሰብ ብር 351.821ሲሆን ለዚሁ ት/ቤት ብቻ ወጪ የሚደረግ ለደመወዝ ብር 205.887 ለስራ ማስኪጃ ደግሞ ብር 30.000 ራሱን ለመቻል ብር 115.934 ገቢ ማስገኘት ይጠበቅበታል፤

አወሊያ ቁጥር2 ነስር ት/ቤት ዘነበ ወርቅ ቅርንጫፍ ከ ኬጅ-2ኛ/ት/ቤት

በአካባቢው ይኖሩ የነበሩት የመሬት ባለይዞታዎች መጀመሪያ ለነስር መስጅድ ውቅፍ አድርግው መጠነኛ መስጅድ በመስከረም 1977 ከገነቡ በኋላ የመስጅድ ት/ቤት በአራት የመማሪ ክፍሎች አረብኛ ትምህርት ተጀመረ። በመቀጠልም የትምህርት አሰጣጡን በማሳደግ የአካዳሚክ ትምህርት ጨምሮ መስጠቱን ቀጠለ። ት/ቤቱ በተለያዩ ድርጅቶች አስተዳደሪነትና የገንዘብ ድጋፍ ሲደረግለትም ነበር። አባድር ትምህርት ቤት፤ኤራን ኤምባሲ፤ኢትዩጵያ መስሊም ልማት ማህበር፤የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዩች ጠቅላይ ም/ቤት፤እንደ ቅደም ተከተላቸው እስከ 1995 ድረስ ሲያስተዳድሩት ቆይተዋል። ከ1995 ጀምሮ አለማቀፉ እስላማዊ እርዳታ ድርጅት (IIRO) ከአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዩች ጠቅላይ ም/ቤት በመረከብ ትምህርት ቤቱን ወደ ሁለተኛ ደረጃ አሳድጎ ሲያስተዳድር ቆይቶ፤ ፍቃዱ ሲሰረዝ ከሰኔ /2003 ጀምሮ ወደ ኢትዩጵያ እስልምና ጉዳዩች ጠቅላይ ም/ቤት ተጠቃለለ።





በአጸደ ህጻናቱ እስከ 150 ተማሪዎች፤በአንደኛ ደረጃ ድግሞ 400 ተማሪዎች እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃው 200 ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተማር ላይ ይገኛሉ፡ በአሁኑ ስዓት ከአጸደ

ህጻናት እስ ሁለተኛ ደረጃ 737 ተማሪዎች ተቀብሎ የሚያስተምር ሲሆን 600 ተማሪዎችን በተመጣጣኝ ክፍያ ቀሪ 137ቱን ደግሞ ሙሉ በሙሉ በነጻ ተቀብሎ በማስተማር ላይ ይገኛል።

በትምህርት ቤቱ 47 መምህራንና 36 ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አሉት። በት/ቤቱ ያለውን የገንዘብ ገቢና ወጪውን በተመለከተም ከተማሪዎች ወርሃዊ ክፍያ የሚሰበሰብ ብር 219.548 ሲሆን ለዚሁ ት/ቤት ብቻ ወጪ የሚደረግ ለደመወዝ ብር 371.423 ለስራ ማስኬጃ ደግሞ ብር30.000 ፤ራሱን ለመቻል ብር 181.875 ገቢ ማስገኘት ይጠበቅበታል፡፤

አወሊያ ኮሌጅ

ኮሌጁ ጥቅምት 1997 በአወሊያ ት/ቤቶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ መሰናዶ ት/ቤት መግባት ያልቻሉትን በዝቅተኛ ክፍያ የትምህርት እድል እንዲያገኙና በአገር አቀፍ ደረጃ የሚታየውን የአረብኛ ቋንቋ ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች በማፍራት በኢትዩጵያና በአረቡ አለም መካከል ድልድይ በመሆን በአገር ልማትና እድገት አስተዋጾ ለማበርከት በማቀድ ህጋዊ እውቅና በማግኘት በሙያና ቴክኒክ ኮሌጁ ማርኬቲንግ፤ አካውንቲንግ፤ህግና አይቲ ዲፓርትመንት እንዲሁም በአረብኛው ኮሌጅ ደግሞ በአርብኛ ቋንቋ ትምህርት በመስጠትና በማስመረቅ ለስራ ያበቃ ኮሌጅ ነው።

ከሰኔ /2003 ጀምሮ ግን ኮሌጅ ሃላፊዎችንና 36 የቦርዲንግ ተማሪዎች እንዲሰናበቱ ከተደረገ በኋላ ኮሌጁ በእጅጉ አግልግሎቱ ተዳክሞ ይገኛል ። የአወሊያ ኮሊጅ ሲነሳ ዶ/ር አብደላ ከድር ፤ ናስር ሻፊና አሁን ደግሞ ኡስታዝ ረመዳን አህመድና ኡስታዛ ፋጡማ ያበረከቱት አስተዋጾ ሁሌም አይረሳም ።

ኮሌጁ በአሁኑ ስአት የሙያና ቴክኒክ ስልጠናውን ሙሉ በሙሉ አቁሞ የአረብኛ ቋንቋ ትምህርት እየሰጠ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ በ2012 የዲግሪ መርሃግብር እንዲሰጥ ከከፍተኛ ትምህርትና ምዘናዎች ኤጀንሲ ህጋዊ አውቅና አግኝቷል። በኮሌጁ 8 መምህራንና 7 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ15 መምህራንና ሰራተኞች አሉ። በት/ቤቱ ያለውን የገንዘብ ገቢና ወጪውን በተመለከተም ከተማሪዎች ወርሃዊ ክፍያ የሚሰበሰብ ብር 14.950 ሲሆን ለኮሌጁብቻ ወጪ የሚደረግ ለደመወዝ ብር 67.101 ለስራ ማስኬጃ ደግሞ ብር 6.522 ራሱን ለመቻል ብር 58.673 ገቢ ማስገኘት ይጠበቅበታል።



አወሊያ ኮሌጅ